# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ

# የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የልኬታዊ
# ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 01/2013

**መስከረም 2014 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
## የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የልኬታዊ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 01/2014

በሀገራችን ኅብረት ሥራ ማህበራት በተለያዩ አይነት እና ደረጃ ተደራጅተው የአባላትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በመፍታት አዎንታዊ አስተዋፅዖ እያበረከቱ የሚገኙ በመሆኑ እና የአባላትን ሀብት፣ ጉልበት እና እውቀት በማሰባሰብ፤ አባላት መሪ፣ ተቆጣጣሪ እና ተጠቃሚ የሆኑበት፤ ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ልዩነት ሳይደረግ በአባላት ሙሉ ፍላጎት የሚመሰርቷቸው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተቋማት በመሆናቸው በህግ አግባብ መምራት አስፈላጊ በመሆኑ፡፡

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥራቸው፣ የሰበሰቡት ቁጠባና የሚሰጡት የብድር አገልግሎት እንዲሁም ሌሎች የፋይናንስ አገልግሎቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ ከብክነት እና ከምዝበራ ነጻ ሆነው በህግ እንዲመሩ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ እና በአባላት፣ በመንግስት እና አበዳሪ አካላት ዘንድ አመኔታ እንዲኖራቸው፣ መልካም ገፅታ እንዲገነቡ፣ ውጤታማ ፣ ስኬታማ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የልኬታዊ ኢንስፔክሽን መመሪያ ማወጣት አስፈላጊ በመሆኑ የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀፅ 4 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት ልኬታዊ ኢንስፔክሽን መመሪያ አወጥቷል፡፡

## FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## COOPERATIVE AGENCY
## SAVING AND CREDIT COOPERATIVE SOCIETIES PRUDENTIAL INSPECTION DIRECTIVE NO 01/9/2021

Cooperatives in our country are organized in various forms and levels and are making a positive contribution by helping to solve the social and economic problems of members. They achieve this by harnessing members' resources, labor and knowledge under the ownership and control of their members.

It is important that they are guided by the law, as they are economic and social institution whose membership is open to all irrespective of race, color, sex, relgion, disability, economic or polticale background. As a consequence it has become essential to manage cooperatives in accordance with law.

The number of savings and credit cooperatives, their savings, loans and other financial services are growing exponentially, thus it is important to ensure that they are guided by law to be free from waste and corruption; so that members, government and lenders have confidence in them; as well as for building a good image. In order to be successful and competitive, it is necessary to issue a world class prudential inspection directive. Accordingly, the Federal Cooperative Agency has issued this prudential inspection directive in accordance with the power given to it under article 52 Sub-Article 4 of cooperative society's proclamation No 985/2016.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ልኬታዊ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 01/2014 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጉም**

በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹት ቃላት እና ሐረጎች የሚከተሉትን ትርጉም ይይዛሉ።

1/ **"አዋጅ"** ማለት የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ነው።

2/ **"ፐርልስ"** ማለት የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራትን የፋይናንስ አፈፃፀም በልኬታዊ አሰራር ኢንስፔክት ለማድረግ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ምክር ቤት የወጣ ማነፃፀሪያ ስታንዳርድ ነው።

3/ **"የፐርልስ ምጣኔ"** ማለት በዓለም አቀፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ምክር ቤት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመለካት የወጣ ዓለም አቀፍ የንፅፅር ቀመር ነው።

4/ **"ልኬታዊ ኢንስፔክሽን"** ማለት በፐርልስ ቀመረ-ስሌት መሠረት የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራትን ኢንስፔክት ማድረግ ነው።

## Part One

## General Provisions

1. **Short title**

This directive can be cited as "The Saving and Credit Cooperative Prudential Inspection Directive No. 01/2021".

2. **Definitions**

Subject to the definitions of the cooperatives proclamation No.985/2016, the words and phrases described in this directive shall have the following meanings, unless the context of the term implies any other meaning.

1/ **"proclamation"** mean the cooperative proclamation No. 985/2016.

2/ **"PEARLS"** means quantitative standards developed by World Council of Credit Unions for prudential inspection of the financial performance of saving and credit cooperatives societies.

3/ **"PEARLS Ratio"** is an international formula developed by the World Council of Credit Unions for prudential inspection of the financial performance of saving and credit cooperatives

4/ **"prudential inspection"** means the inspection of saving and credit cooperatives in accordance with PEARLS formulas.



Cooperative Agency

5/ **"ኢ-ልኬታዊ ኢንስፔክሽን"** ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በሚገኙበት ቦታ ላይ በመገኘት ህግንና አሰራርን መሠረት አድርጎ በተዘጋጀ ቼክ-ሊስት በመጠቀም ገላጭ በሆነ መንገድ ኢንስፔክት ማድረግ ነው፡፡

6/ **"ኢንስፔክተር"** ማለት አግባብ ባለው ባለስልጣን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የኢንስፔክሽን ስራ ለማከናውን የተመደበ ባለሙያ ነው፡፡

7/ **"የሃብት ጥበቃ"** ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ሃብት ወይም ንብረት በአግባቡና በስርዓት መጠበቅ ነው፡፡

8/ **"ውጤታማ የፋይናንስ አወቃቀር"** ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለዕድገት ወሳኝ የሆኑ፣ ገቢ የሚያመነጩ እና የፋይናንስ አቅማቸውን ለማሳደግ የሚያስችላቸውን ተገቢና ተመጣጣኝ ሃብት መመደብ ነው፡፡

9/ **"የሃብት ጥራት"** ማለት በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ትርፍ የማያስገኙ ሃብቶች በትርፍ ግኝት ላይ የሚያስከትሉት ጫና እና የክፍያ አቅም ማነፃፀሪያ ማለት ነው፡፡

10/ **"የገቢና ወጪ ምጣኔ"** ማለት እያንዳንዱ ሃብት ያስገኘውን ውጤት እና ያስከተለው ወጪ ለመገምገም የሚረዳ ምጣኔ ነው፡፡

11/ **"የመክፈል አቅም"** ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ላለበት ዕዳ ወይም ለሚሰጠው ብድር በወቅቱና በተፈለገው ጊዜ ለገንዘብ ጠያቂዎች ወይም ለአባላት ክፍያዎች የመፈፀም አቅም

5/**"Non prudential inspection"** means on-site inspection of saving and credit cooperatives using a check-list based on the rules and regulations with more limited numerical measurements.

6/ **"Inspector"** means a professional assigned by the appropriate authority to carry out inspections of saving and credit cooperatives.

7/**"Asset protection"** means appropriate and systematic protection of the assets of saving and credit cooperatives.

8/**"Effective financial structure"** means assigning appropriate and sufficient resources that are crucial for development, income generation and financial strength of saving and credit cooperative societies

9/**"Asset quality"** means the real value of the cooperative's assets. An effective management of cash so that it can meet deposit withdrawal requests and liquidity reserve requirements.

10/ **"Rates of return and costs"** means a standard used to evaluate the incurred cost and returns of each investment.

11/ **"Liquidity"** means an effective management of cash so that it can meet deposit withdrawal requests and liquidity reserve requirements.



Cooperative Agency

የሚገመገምበት አሰራር ነው፡፡

12/ **"ዕድገት"** ማለት ወቅታዊ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሚታዩ ዋና ዋና የሂሳብ ርዕሶች እና በአባላት ቁጥር የተገኘ ለውጥ ቀደም ሲል ከነበረው የሂሳብ ዘመን ውጤት ጋር ሲነፃፀር የተፈጠረ ልዩነት ነው፡፡

13/ **"ድንገተኛ ኢንስፔክሽን"** ማለት ጥያቄ ሲቀርብ ወይም መታየት አለበት ተብሎ ከታመነ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ሳያሳውቁ የሚደረግ ኢንስፔክሽን ነው፡፡

14/**"መደበኛ ኢንስፔክሽን"** ማለት በዕቅድ ተይዞ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማሳወቅ የሚደረግ ኢንስፔክሽን ነው፡፡

15/ **"በመስክ ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን** "ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በሚገኙበት ቦታ ላይ በመገኘት የሚደረግ ኢንስፔክሽን ነው፡፡

16/ **"በመስክ ላይ ሳይገኙ የሚደረግ ኢንስፔክሽን"** ማለት አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃዎችን ቀድሞ እንዲደርሰው በማድረግ በቦታው ላይ መገኘት ሳያስፈልግ የፐርልስምጣኔዎችን በመጠቀም አፈፃፀሙን መለካትና መተንተን ነው፡፡

17/ **"ግብረ-መልስ"** ማለት የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክተሮች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት ካደረጉ በኂላ የተገኙ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት መወሰድ የሚገባቸውን

12/ **"Growth"** means increment in each of the most important account lines on the financial statements, as well as growth in membership where the indicators are measured by comparing current year results with previous one.

13/**"Emergency inspection"** means an inspection done without informing the saving and credit cooperative societies when the request is made or inspection is deemed necessary.

14/**"Regular inspection"** means a planned inspection of the saving and credit cooperative societies.

15/**"On-site inspection"** means prudential inspection by being physically present at the site of the saving and credit cooperative

16/ **Off-site inspection"** means prudential inspection done based on prescribed financial documents submitted by saving and credit cooperatives without being physically present at the site of the saving and credit cooperative.

17/**"Feedback"** means recommendations given after prudential inspection upon identification of the strengths and weaknesses of the saving and credit cooperatives societies consisting of measures to be taken given by the inspector




የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Cooperative Agency

እርምጃዎች በማመላከት በቃል እና በፅሁፍ የሚሰጥ ነው።

18/ **"ለማይመለስ ብድር የማካካሻ ክፍያ"** ማለት በሂሳብ አቋም መግለጫ ውስጥ የተሰራጨ ብድር ትክክለኛ ዋጋ በትክክል እንዲታይ ከመነሻው የተቀመጠ የተወሰነ የማካካሻ የገንዘብ መጠን ነው።

19/ **"ያልተመለሰ ብድር"** ማለት ማንኛውም የተሰራጨ ብድር ሆኖ መመለስ ከሚገባው የውል ቀን በኋላ ሳይከፈል የቀረ ብድር ነው ።

20/ **"ከስራ ማገድ"** ማለት የኅብረት ስራ ማህበሩ ኢንስፔክት ሲደረግ በሚያሳየው ክፍተት መሰረት የስራ በታውን ማሸግ፣የባንክ አካውንቱን ማገድ ነው።

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1/ ህግና አሰራርን አክብረው በመስራት የአባላትን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ፤ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ የላቀ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ውጤታማና ተወዳዳሪ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለመፍጠር፤

2/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን በልኬታዊ ኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት በማድረግ የተሻሉትን ለማስቀጠል እና ችግር ያለባቸውን አሰራሮች ቀድሞ በመለየት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለመከላከልና ለመቀነስ ነው።

3/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን

orally and in writing.

18/ **"Allowance for loan loss"** means an amount set aside in a statement of financial position so that the true value of the loan portfolio is fairly shown.

19/ **"Delinquent loans"** means any loan of which the principle or interest remain unpaid after the due contractual date.

20/ **"Suspended from its activities"** means based on inspection feedback, the findings of risk and weaknesses related to the saving and credit cooperative, its working office shall be closed and its bank account suspended.

## 3. <u>Purpose of the directive</u>

1/ To create competent and competitive saving and credit cooperatives that will contribute significantly to the building of the country's economy; and ensure the benefit to the members by respecting the law and practice;

2/ In order to maintain the best of the saving and credit cooperatives, to identify problems in their practices and to take corrective measures in advance, and in accordance with the prudential inspection system to prevent and reduce risks.

3/ To strengthen the trust of the members, the



Cooperative Agency

በልኬታዊ ኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት በማድረግ በአባላት፣ በህዝቡ እና በመንግስት ዘንድ ተዓማኒነታቸውን ለማጎልበት ነው።

4. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጅ መሠረት በሀገሪቱ በተደራጁ እና በልኬታዊ ኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት እንዲደረጉ አግባብ ባለው ባለስልጠን በተለዩ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

5. <u>የልኬታዊ ኢንስፔክሽን መሰረታዊ መርሆዎች</u>

ልኬታዊ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት ኢንስፔክሽን የሚከተሉት መሰረታዊ መርሆች ይኖሩታል፡-

1/ መሻሻል ላይ ትኩረት ማድረግ፣
2/ ውጤት ላይ ማተኮር ፣
3/ ችግር ላለባቸው አሰራሮች ትኩረት መስጠት፣
4/ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ የማይጥሱ ፈጠራን እና የአሰራር ልዩነቶችን ማበረታታት፣
5/ ትክክለኛ መረጃን መጠቀም፣
6/ ለውሳኔ የሚረዱ መስፈርቶችን መጠቀም፣
7/ ግልጽ አሰራር መከተል፣
8/ ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ መሆን፣
9/ አሰራሮችን ከልምድ ማሻሻል፣
10/ የውስጥ ቁጥጥርን ማበረታታት፣

public and the government by inspecting the saving and credit cooperatives through a prudential inspection system

**4.<u>Scope of application</u>**

This directive shall apply to saving and credit cooperative societies established under proclamation and designated for prudential inspection by the appropriate authority.

**5. <u>Principles of Prudential Inspection</u>**

Prudential saving and credit inspection shall have the following basic principles:-

1/ Focus on improvement
2/ Focus on the outcome
3/ Be proportionate to risk
4/ Encourage legal innovation and diversity
5/ Use accurate impartial evidence
6/ Disclose the criteria used for judgment
7/ Be open about the process
8/ Give attention to value for money
9/ Improve practice based on experience
10/ Encouraging internal control



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዝገብ ቤት
Archive
Cooperative Agency

## ክፍል ሁለት

## ስለ ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክሽን

### 6. አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት ፡-

አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ በዓለም አቀፍ ደረጃ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክት ከሚደረጉባቸው ውስጥ ተስማሚ የሆኑትን የልኬታዊ ኢንስፔክሽን ስታንደርድ ይመርጣል ወይም አዳዲስ ስታንደርዶችን ያዘጋጃል ፡፡

2/ በአዋጅ አንቀጽ 52 መሠረት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት የሚያደርግ የሥራ ክፍል ያደራጃል፣ ባለሙያዎችን ይመድባል፡፡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራትን የደረጃ መስፈርት በማዘጋጀት በደረጃ ይለያል፡፡

3/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት የሚያደርጉ ባለሙያዎችን በሥራው ላይ ከመሰማራታቸው በፊት እና ሥራ ላይ እያሉ ያለባቸውን የዕውቀትና የክህሎት ችግር በመለየት አቅማቸውን ይገነባል፡፡

4/ አግባብ ያለው ባለስልጣን በማንኛውም ጊዜ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት ማድረግ ይችላል፡፡

## PART TWO

## Saving and Credit Cooperatives Inspection

### 6. The duties and responsibilities of the appropriate authority

The duties and responsibilities of the appropriate authority shall be as follows:-

1/ At the international level, saving and credit cooperatives are inspected through prudential standards; Of these, the most appropriate ones shall be selected and potentially revised, setting new standards where deemed appropriate.

2/ In accordance with Article 52 of the Proclamation, it shall organize a working unit and assign experts to inspect saving and credit cooperatives, and rank saving and credit cooperatives by establishing ranking criteria.

3/ Experts who have the responsibility to undertake saving and credit cooperatives inspection shall be trained, both before engagement in the inspection activities and on a continuous basis afterwards by identifying the knowledge and skills gaps of the inspectorat.

4/ The appropriate authority may carry out a prudential inspection of a saving and credit cooperative at any time.



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Archive
Cooperative Agency

5/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም አባላት ሲጠይቅ ኢንስፔክት ያደርጋል።

6/ ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኢንስፔክት መደረግ አለበት።

7/ ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ኢንስፔክት የሚደረገው በተመደበው ወይም በተመደቡ ሕጋዊ ኢንስፔክተር ወይም ኢንስፔክተሮች ብቻ ይሆናል።

8/ በልኬታዊ የኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት የሚደረጉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክት የሚደረጉት በፌደራል ወይም በክልል ወይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወይም በድሬደዋ አስተዳደር ደረጃ በተደራጁ ወይም በተመደቡ ኢንስፔክተሮች ብቻ ይሆናል።

9/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሻለ አሰራር መኖሩ ሲረጋገጥ አግባብ ያለው ባለስልጣን በልኬታዊ ኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት ሊያደርግ የሚችል ተቋም ሊያደራጅ ወይም ባለሙያ ሊመድብ ይችላል።

10/ ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተመደበ የኅብረት ሥራ ማህበር ኢንስፔክተር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ልኬታዊ ወይም ኢ-ልኬታዊ ወይም ሁለቱንም የኢንስፔክሽን አሰራር በአንድ ላይ

5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (4) the appropriate authority shall conduct an inspection of a saving and credit cooperative at the request of its management committee or its members when the majority of the executive committee or one third of the total members or their representatives make this request.

6/ Saving and credit cooperative societies that are subject to prudential inspection shall be inspected at least once a year.

7/ Saving and credit cooperative societies that are subject to prudential inspection shall be inspected only by the designated legal inspectors.

8/ Saving and credit cooperative societies that are subject to prudential inspection shall be inspected only by inspectors organized at the federal and regional state, the Addis Ababa City Administration and Diredewa Administration levels.

9/ Subject to the provisions of sub-article (8) of this Article, the appropriate authority may establish an institution that may conduct inspections through a quantitative inspection system or appoint an expert.

10/ A prudential cooperative inspector may inspect the saving and credit cooperatives using prudential or non-prudential inspection or both simultaneously.



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Cooperative Agency

በመጠቀም ኢንስፔክት ሊያደርግ ይችላል፡፡

11/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በልኬታዊ ኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት የሚደረጉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አግባብ ባለው ባለስልጣን በተዘጋጀው የፐርልስ ምጣኔዎች መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢ-ልኬታዊ አሰራር ኢንስፔክት የሚደረጉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አግባብ ያለው ባለስልጣን ባወጣው ኢንስፔክሽን መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

13/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 12 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢ-ልኬታዊ አሰራር ኢንስፔክት የሚደረጉ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት ትኩረት የሚያደርገው አደረጃጀት እና ምዝገባ፣ ስራ-አመራር፣ የሥራ አፈጻጸም ወይም አሰራርን፣ የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን እና የሰርተፊኬሽን ግብረ-መልስ እና ሪፖርቶችን፣ አለመግባባት አፈታት ይሆናል፡፡

14/ ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን ስራ የተመደበ የኢንስፔክሽን ባለሙያ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት ለማድረግ ሲንቀሳቀስ ማንነቱን እና ኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን እንደተላከ የሚገልጽ ደብዳቤ አግባብ ካለው ባለስልጣን ማግኘት አለበት፡፡

15/ ኢንስፔክተሩ የኢንስፔክሽን ሥራውን ከመጀመሩ

11/ Subject to the provisions of sub-article 10 of this article, the saving and credit cooperatives that are inspected by the prudential inspection procedure shall be prepared only in accordance with the PEARLS ratios set by the appropriate authority.

12/ Subject to the provisions of sub-article (10) of this article, saving and credit cooperatives to be inspected by a non-prudential method shall be subject to the inspection directive issued by the appropriate authority.

13/ Without prejudice to the provisions of sub-article 12 of this article, saving and credit cooperatives which are inspected non-prudentially may focus on the organization and registration, management, performance or operations, audit, inspection and certification feedback and reports, and the resolution of disputes.

14/ A prudential inspection professional shall be received a letter from the appropriate authority stating that s/he has been sent to perform the inspection of saving and credit cooperatives.

15/ A prudential inspection professional, before the commencement of the inspection work, shall inform the cooperative management



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Cooperative Agency

በፊት በኢንስፔክሽኑ ላይ ለተገኙት የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አመራሮች እና ባለሙያዎች የኢንስፔክሽኑን ዓላማ አስመልክቶ ገለጻ ማድረግ አለበት፡፡

16/ ኢንስፔክሽኑን በተመለከተ ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች ኢንስፔክተሩ ተገቢውን መልስ እና ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡

17/ ኢንስፔክተሩ ኢንስፔክት ያደረገውን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በቦታ ላይ በመገኘት የኢንስፔክሽን ሥራውን የሚያካናውን ከሆነ ሥራውን እንደጨረሰ በቦታው ለተገኙ አካላት የቃል ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡

18/ ኢንስፔክተሩ የልኬታዊ የኢንስፔክሽን አሰራርን ተከትሎ ኢንስፔክት ሲያደርግ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የቀረቡለት አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ምንጮች ላይ የተቀመጡ የሂሳብ መረጃዎችን በስታንደርዱ መሠረት የመቀየር ወይም ተሰርቶ ቀርቦ ከሆነ ትክክል ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

19/ ኢንስፔክተሩ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት ካደረገበት ቀን ጀምሮ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሕጋዊ የሆነ የጽሑፍ ግብረ-መልስ፤ መወሰድ የሚገባውን የቅጣት ዓይነት በመለየት እና በመጥቀስ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ መላክና መድረሱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

20/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ 17 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚወሰደውን የእርምት ቅጣት

committee, its representatives and experts present, of the purpose of the inspection.

16/A prudential cooperative inspector shall provide an appropriate answer and explanation to any relevant questions raised by the participants

17/If the inspection officer performs the inspection work the saving and credit cooperative, the inspector may provide verbal feedback to those present on the site and at the time of completion.

18/ A prudential cooperative inspector shall be responsible for verifying the accuracy and completeness based on the source documents of the accounting records provided by the cooperative in accordance with the standard inspection procedures of saving and credit cooperatives.

19/ Any cooperative inspector after inspecting the saving and credit cooperative shall send legal feedback to the cooperative within one month from the date of inspection specifying the type of penalty to be taken, and send it to the cooperative and ensuring that it is received.

20/ Subject to the provisions of sub-article 17 of this Article, the type of corrective action to be



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዝገብ ቤት
Archive
Cooperative Agency

ዓይነት በደብዳቤ ከግብረ-መልስ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

21/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 19 እና 20 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንስፔክሽን ግብረ-መልስ ለመከታተል እና ተግባራዊ ለማድረግ እንዲመች ለሚመለከታቸው አካላት በግልባጭ እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት፡፡

## 7. የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር መብትና ግዴታ፡-

1/ ማንኛውም ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ልኬታዊ ኢንስፔክሽን አስመልክቶ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ) አግባብ ያለው ባለስልጣንን የኢንስፔክሽን አገልግሎት እንዲሰጠው የመጠየቅ፣

ለ) በኢንስፔክሽኑ ወቅት ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮችን ኢንስፔክተሩ ግልጽ እንዲያደርግለት ማብራሪያ የመጠየቅ፣

ሐ) ኢንስፔክት ሊያደርግ የመጣውን ኢንስፔክተር ሕጋዊነቱን የሚገልጽ መረጃ እንዲሰጠው የመጠየቅ፣

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የኢንስፔክሽን ሪፖርት የማግኘት፣

ሠ)የኢንስፔክሽን ግብረ-መልስ ላይ ቅሬታ ካለው ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ሠ አግባብ የሚቀርብ ቅሬታ መጀመሪያ ለኢንስፔክተሩ የቅርብ ኃላፊ ያቀርባል፤ ቅሬታው ካልተፈታ ለሚቀጥለው የበላይ

taken shall be provided in writing along with the feedback.

21/ Subject to the provisions of sub-articles 19 and 20 of this article, the inspection feedback shall be made available to the concerned bodies in order to facilitate the monitoring and implementation.

## 7. The rights and obligations of saving and credit cooperative societies

1/ Saving and Credit Cooperative societies have the following rights regarding prudential inspection which include:-

a) Requesting the appropriate body for inspection services;

b) Asking for an explanation from the inspector to clarify issues that are not clear during the inspection;

c)Requesting the inspector to provide information on his/her identity and legitimacy of mandate to inspect;

d) To receive the inspection report of the cooperative;

e) If there is a complaint about the inspection to apply to the concerned body;

2/ Subject to the provisions of sub-article 1(e) of this article; the grievance procedure shall first be submitted to its senior supervisor. If the

ኃላፊ የሚቀርብ ሆኖ በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ኃላፊዎች የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

3/ ማንኛውም ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ኢንስፔክሽንን አስመልክቶ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩን ማንኛውንም ስራ ኢንስፔክት የማስደረግ፤

ለ) በኢንስፔክሽኑ ወቅት የሚያስፈልጉ እና የተጠየቁ ትክክለኛና ተዓማኒነት ያላቸው መረጃዎችን የማቅረብ፣

ሐ) በኢንስፔክተሩ የሚጠየቁትን ጥያቄዎች ግልጽ መረጃ መስጠት እና ማብራራት፣

መ) በኢንስፔክሽን ሥራው ላይ እንዲገኙ የሚፈለጉ አካላትን የማቅረብ፣

ሠ)ቅሬታ የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንስፔክሽን ግብረ-መልሶችን እና የተሰጡ የማስተካከያ እርምጃዎችን ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ ፣

4/በልኬታዊ ኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት የሚደረግ ማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚከተሉትን መረጃዎች በተጠቀሰው ጊዜ ኢንስፔክት ለሚያደርገው አግባብ ላለው በለስልጣን ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡-

ሀ) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩን የሃብትና

complaint is not resolved, it will be submitted to the next level and the decision will be made by the state or city administration department of cooperatives or the Federal Cooperative Agency.

3/ Any saving and credit cooperative shall have the following obligations regarding to prudential inspection

a) Inspect any performance of the saving and credit cooperative.

b) Provide accurate and reliable information as required during the inspection

c) Provide clear information and clarify questions to the inspector;

d) Ensure that the staff and officers of the cooperative make themselves available as required during the inspection work;

e) Subject to the right of appeal, accept and implement inspection feedback and recommended corrective measures.

4/ Any saving and credit cooperative that is inspected by the prudential inspection System shall submit the following information to the inspection body within the specified time.

a) The saving and credit cooperative shall submit in the prescribed form, a statement its assets and debt, the income and expenditure

ዕዳ፣ ገቢና ወጭ መግለጫ፣ የብድር አመላለስ መግለጫ እና የተሰራጨ ብድር ሪፖርት በ6 ወር አንድ ጊዜ ያቀርባል፤ አግባብ ያለው ባለስልጣን ኢንስፔክተር ሪፖርቱን ተንትኖ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

ለ) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩን ትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት፣ የገቢ ምንጭ መግለጫ፣ የገንዘብ ፍሰት መግለጫ፣ ጥሬ ገንዘብ እና ዕጣ ላይ የተደረጉ ለውጦች መግለጫ፣ የማይመለስ ብድር መጠባበቂያ፣ የአባላት ቁጥር መግለጫ እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ሪፖርት በዓመት አንድ ጊዜ ማቅረብ አለበት፣ አግባብ ያለው ባለስልጣን ኢንስፔክተር ሪፖርቱን ተንትኖ ግብረ መልስ መስጠት አለበት፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ሀ እና ለ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚቀርቡ ሪፖርቶች 6 ወሩ ወይም አመቱ እንዳለቀ 10 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለባቸው፣

ረ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ሐ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ አዘግይቶ ሪፖርት ያቀረበ ለመጀመሪያው ዙር አስር ቀናት፣ለሁለተኛው ዙር አስር ቀናት እና ለሶስተኛ ዙር አስር ቀናት ተሰጥቶት የማያቀርብ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 በተደነገገው መሠረት ይቀጣል፣

statement, the loan statement and disbursement report once every 6 months; the appropriate authority's inspectorate authority inspector shall analyze the reports and provide feedback.

b) The saving and credit cooperative shall submit the profit and loss statement, the audit report, the source of income, the cash flow statement, cash and share changes statement, allowance for loan losses summary statement, the membership number statement and other useful information once a year and the appropriate authority inspector shall analyze the report and provide feedback;

c) Subject to the provisions of sub-article 4(a) and (b) of this article, reports must be submitted no later than 10 days after the end of a 6 month or a year.

d) Subject to the provisions of sub-article 4(c) of this article, the cooperative saving and credit cooperative, which has been given ten days for the first round, ten days for the second round and ten days for the third round, who does not submit a report, shall be punished in line with article 19 and measures shall be taken,



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዝገብ ቤት
Archive
Cooperative Agency

## ክፍል ሶስት

## የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ልኬታዊ በሆነ አሰራር ኢንስፔክት ስለማድረግ

### 8. የልኬታዊ ኢንስፔክሽን ምጣኔ

ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተመረጠ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በተመረጡ የፐርልስ ምጣኔዎች መሠረት ኢንስፔክት ይደረጋሉ

### 9. የሃብት ጥበቃ ምጣኔ ኢንስፔክት ስለማድረግ፡-

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሃብት ጥበቃ ምጣኔ ኢንስፔክሽን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት

1/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ሃብት ወይም ንብረት በአግባቡና በስርዓት ጥበቃ መደረጉን፣

2/ የተሰራጨ ብድር አመላለስ የሚገኝበትን ደረጃ በየጊዜው ክትትል መደረጉ ፣

3/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በጊዜው የሚመለሱ እና የማይመለሱ ብድሮችን በመለየት የብድር አመላለስ ውጤታማነት ማሳደጉን፣

4/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የመመለሻ ጊዜው አስራ ሁለት ወራት እና ከዚያ በላይ ላለፈው ብድር ሙሉ በሙሉ መተካት የሚችል የገንዘብ መጠን የወለድ ምጣኔ ላይ በማካተት በቂ መጠባበቂያ ገንዘብ ማስቀመጣቸውን ማረጋገጥ፣

5/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የመፍረስ አደጋ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ሊኖራቸው የሚገባ የሃብት መጠን የአባላት ቁጠባንና ዕጣን ሙሉ

## PART THREE

## Inspection of saving and credit cooperatives in a prudential inspection

### 8. Prudential Inspection Ratio Standards

Saving and credit cooperatives designated by the appropriate authority for prudential inspection shall be inspected in accordance with the selected PEARLS ratio and Standards.

### 9. Inspect Asset Protection Ratios

The saving and credit cooperatives asset protection ratio inspection shall focus on the following to ensure;-

1/Saving and credit cooperatives' assets and property shall be properly and systematically protected.

2/ The status of disbursed loans of saving and credit cooperatives are monitored regularly..

3/ Increase saving and credit cooperatives credit efficiency by identifying timely repayment and non-repayment of loans.

4/ Ensure that saving and credit cooperatives have a sufficient reserve amount including the interest for the last twelve months or more of the previous loan.

5/ The amount of asset that saving and credit cooperatives should have in the event of a bankruptcy should be enough to fully cover members' saving and shares ,and hold at least



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዛግብት ቤት
Archive
Cooperative Agency

በሙሉ ሽፍኖ ቢያንስ አስር ከመቶ ቀሪ ትርፍ ገንዘብ መኖሩን፣

10. <u>ውጤታማ የፋይናንስ አወቃቀር ኢንስፔክት ስለማድረግ</u>፡-

ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ የፋይናንስ አወቃቀር ኢንስፔክሽን ከዚህ በታች የተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤

1/ማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከአጠቃላይ ሃብቱ ውስጥ ከሰባ እስከ ሰማንያ በመቶ የሚሆነውን ለብድር አገልግሎት ማዋሉን፣

2/ ማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለድንገተኛ ወጪዎች በገንዘብ መዋዕለ ንዋይ ላይ የሚያውለው ሃብት ከአጠቃላይ ሃብቱ ከሃያ በመቶ አለመብለጡን፣

3/ማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ከአጠቃላይ ሃብቱ ውስጥ ከሰባ እስከ ሰማንያ በመቶ የሚሆነው የፋይናንስ ምንጭ የአባላት ቁጠባ ድርሻ መሆኑን ፣

4/ የማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የተቋማዊ ካፒታል ድርሻ ከአጠቃላይ ሃብቱ ውስጥ ቢያንስ አስር በመቶ መሆኑን፣

5/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ የፋይናንስ አቅማቸውን ለማጠናከርና ራሳቸውን እንዲችሉ የተለያዩ የቁጠባ ማሳደጊያ ስልቶችን በመንደፍ እና ተግባራዊ በማድረግ የሚሰበስቡትን የቁጠባ መጠን ማሳደጋቸውን፣

6/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት

ten percent surplus money.

**10. <u>Inspect effective financial structure</u>**

Effective financial structure inspection of saving and credit cooperatives shall focus on the following issues and shall ensure

1/ Any saving and credit cooperative society shall allocate 70% up to 80% of its total assets to loan;

2/ Any saving and credit cooperative society shall invest in emergency expense of not more than 20% of the total asset;

3 /Any saving and credit cooperative society shall have 70% up to 80% of the source of funding of its total assets from membership saving;

4/ Any saving and credit cooperative society shall have institutional capital share of at least 10% of its total asset;

5/ Any saving and credit cooperative society shall increase their saving by designing and implementing various saving strategies to strengthen their internal financial capacity and become self-sufficient;

6/Any saving and credit cooperative society shall increase loan disbursement and



Cooperative Agency

የሚሰራጭ የብድር መጠንን ማሳደጋቸውና የብድር አመላለስ ማሻሻላቸውን፣

7/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ አባላት በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሰማሩ የምክር አገልግሎት እና ሙያዊ ድጋፍ ማድረጋቸውን፣

8/ በአባላት ፍላጎት መሠረት የተለያዩ የቁጠባና ብድር አገልግሎት አይነቶችን ማስፋፋት እና ውጤታማ የቁጠባ አሰባሰብ ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ማድረጋቸውን፣

9/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የቁጠባ ባህል ለማሻሻል እና መጠኑን ለማሳደግ፣እንዲሁም የብድር አጠቃቀም እና አመላለስን ለማሻሻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የፋይናንስ ክህሎት ስልጠና መስጠቱን፤

**11.** **<u>የሃብት ጥራት ኢንስፔክት ስለማድረግ</u>**

ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሃብት ጥራት ኢንስፔክሽን ከዚህ በታች በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤

1/ ማንኛውም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ሃብት ወይም ንብረት ገቢ በሚያስገኙ ተግባራት ላይ መዋሉን መለካት

2/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የተሰራጩ ብድሮችንና የማይመለሱ ብድሮችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ክትትል በማድረግ

improve credit flow within prudent limits;

7/ Any saving and credit cooperative society shall provide counselling and professional support to the members of the credit service to engage in various income-generating activities;

8/ According to the needs of the members and taking into consideration the sustainability of the savings and credit cooperative, saving and credit cooperatives shall expand various types of saving and loan services and implement effective saving collection strategies;

9/ Any saving and credit cooperative society shall deliver financial skills training in collaboration with relevant bodies to improve and increase the saving of members, as well as to improve the use and transfer of loans.

**11. <u>Inspect Asset Quality Assurance</u>**

Asset quality assurance inspection of saving and credit cooperatives shall focus on the following issues and shall ensure

1/ Any saving and credit cooperative societies shall measure the quality of its assets based on the income and use of its resources;

2/ Any saving and credit cooperative societies shall effectively monitor disbursed loans and non-performing loans;

ማስመለሳቸውን፤

3/ በውሉ መሠረት የመመለሻው ጊዜው ከደረሰው የተሰራጨ ብድር መጠን ውስጥ በጊዜው የማይመለስ ብድር መጠን ከአምስት በመቶ አለመብለጡን፤

12. <u>የገቢና ወጪ ምጣኔ ኢንስፔክት ስለማድረግ</u>

ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የገቢና ወጪ ምጣኔ ኢንስፔክሽን ከዚህ በታች የተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤

1/ ለኪሳራ ተጋላጭ እንዳይሆን የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን በአግባቡ መመራቱን፤

2/ አስተዳደራዊ ወጪ ከጠቅላላ ሃብቱ ከአምስት በመቶ አለመብለጡን፤

13. <u>የክፍያ አቅም ኢንስፔክት ስለማድረግ</u>

ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የክፍያ አቅም ኢንስፔክሽን ከዚህ በታች የተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤

1/ ከአባላት ለሚቀርቡ የተለያዩ የአገልግሎት ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ ለመስጠትና ከአባላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እንዲጠናከር የመክፈል አቅሙን ማጠናከሩን፣

2/ በአንድ ወር ውስጥ የሚወጡ ሂሳቦችን ከጠቅላላ ቁጠባው በመቀነስ የጠቅላላ ቁጠባውን ቢያንስ አስራ አምስት ከመቶ የሚሆነውን በኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ውስጥ ማስቀመጡን፣

3/ Any saving and credit cooperative societies shall, In accordance with the contract, make sure that loan arrears is not exceeding 5% of the total loan portfolio outstanding.

**12. <u>Inspection Rate of Return and Cost</u>**

The rate of return and cost inspection of saving and credit cooperatives shall focus on the following issues and shall ensure

1/ Any saving and credit cooperative society shall manage the operating expenses so that it is not at risk of bankruptcy;

2/ Any saving and credit cooperative society shall make sure that its administrative expenses do not exceed 5% of its total assets.

**13. <u>Inspect Liquidity</u>**

Liquidity inspection of saving and credit cooperatives shall focus on the following issues:

1/ The saving and credit cooperatives shall strengthen their ability to respond quickly to various service requests from members and strengthen their relationship with members;

2/ Any saving and credit cooperative society shall subtract payments to be made within one month from total saving and put in the account of the cooperative equivalent to at



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Archive
Cooperative Agency

14. <u>እድገት አመላካች ኢንስፔክት ስለማድረግ</u>

ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር እድገት አመላካች ኢንስፔክት በሚደረግበት ጊዜ የአባላት እድገት በየአመቱ ከአስራ ሁለት በመቶ ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

least fifteen percent of the total saving.

**14. <u>Inspect growth indicators</u>**

The inspection of saving and credit cooperatives growth indicators shall ensure that the growth of number of members is not less than twelve percent per annum.



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ

## ክፍል አራት

## ስለ ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የልኬታዊ ኢንስፔክሽን የመረጃ ምንጮችና የአተገባበር ስልቶች

**15. የልኬታዊ ኢንስፔክሽን የመረጃ ምንጮች**

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የልኬታዊ ኢንስፔክሽን የመረጃ ምንጮች የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል፡-

1/ የሃብትና ዕዳ መግለጫ ሪፖርት፣

2/ የገቢና ወጭ መግለጫ ሪፖርት፣

3/ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት፣

4/ ጊዜው ደርሶ ያልተመለሰ ብድር መግለጫ ሪፖርት፣

5/ የጥሬ ገንዘብ፣ በቀላሉ ወደ ጥሬ ገንዘብ ሊለወጡ በሚችሉና በማይችሉ ንብረቶች አመዳደብ እና አያያዝ ሪፖርት፣

6/ የነባር እና በዓመቱ አዲስ የገቡ አባላት ሪፖርት

7/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ከ1 እስከ 6 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆኖ አግባብ ያለው ባለስልጣን በተመደበው ኢንስፔክተር ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን ሥራው የሚያስፈልጉ ተጨማሪ መረጃዎችን መጠየቅ ይችላል፡፡

**16. የልኬታዊ ኢንስፔክሽን አተገባበር ስልቶች**

ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የተለየ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የኢንስፔክሽን አተገባበር ስልቶች እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በሚገኝበት ቦታ ላይ በመገኘት የሚደረግ ኢንስፔክሽን

## PART FOUR

## SOURCES OF INFORMATION ON SAVING AND CREDIT COOPERATIVES AND IMPLEMENTATION STRATEGIES FOR PRUDENTIAL INSPECTION

**15. Prudential Inspection Sources Document**

In order to implement asystem of prudential inspection for saving and credit cooperatives, the following are routine requirments and sources:-

1/ The balance sheet report;

2/ The statement of income and expenditure report;

3/ The profit and Loss report;

4/ The delinquent loan report;

5/ The classification and management of cash, assets that can easily be converted in to cash and that cannot be converted into cash report;

6/ The report of existing and new members

7/ Subject to the provisions of sub-article 1 to 6 of this article, the appropriate authority may request additional information required for the prudential inspection.

**16. Prudential inspection implementation strategies**

Prudential inspection implementation strategies for saving and credit cooperatives shall be as follows:-

1/ On-Site inspection of saving and credit



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዝገብ ቤት
Archive
Cooperative

የሚከተሉትን ጉዳዮች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡-

ሀ) የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክሽን እንደሚፈለገው ዓላማ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ኢንስፔክት ሊደረግ ይችላል፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክተሩ ኢንስፔክት የሚደረገውን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ሊያሳውቅ ወይም ላያሳውቅ ይችላል፣

ሐ) በኢንስፔክሽን ላይ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ዋና ወይም ምክትል ሰብሳቢ ወይም የቦርድ ሰብሳቢ ወይም ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም አባል፣ የብድር ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም አባል፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ተወካይ ወይም ቅጥር ሰራተኛ እና ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክተሩ የሚፈልጋቸው አካላት መገኘት አለባቸው፡፡

መ) ለኢንስፔክሽኑ ወቅት የሚፈለጉ አካላትና የመረጃ ምንጭ ሳይሟላ ወይም ሳይገኝ ኢንስፔክት ማድረግ አይቻልም፡፡

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ 1 መ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢንስፔክሽኑ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎች እና ግለሰቦች ካልተገኙ በቀጣይ 7 ቀናት ውስጥ እንዲገኙ እና የኢንስፔክሽን ሥራው እንዲሰራ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ ቀን ውስጥ በድጋሜ የማይገኝ ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 ንዑስ አቀጽ 1 ፣2 ፣ 3 እና 4 ላይ በተደነገገው መሠረት ቅጣት ይቀጣል፡፡

cooperatives should be based on the following:

a) Saving and credit cooperative inspection may involve a full or partial inspection as required;

b) The cooperative inspector may or may not inform the inspection of the saving and credit of the cooperative in advance;

c) The chairman of the board of directors of the saving and credit cooperative, the secretary, the treasurer, the chairman or member of the control committee, the credit committee chair or member, the manager or the representative, the employee accountant and other cooperatives personnel as required by the inspector must be available;

d) It is not possible to inspect without the presence of the required individuals and sources of information being available during the inspection;

e) Subject to the provisions of sub-article 1 (d) of this article, if the required information and individuals are not available during the inspection, the inspection shall be carried out within the next 7 days. However, if the individual is not present again on this date, action shall be taken in accordance with the provisions of articles 20 sub article 1,2,3,4 of this directive;



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Archive
Cooperative Agency

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክተር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ኢንስፔክት ሲያደርግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ ከ1 እስከ 7 ያሉትን የመረጃ ምንጮችን ማየት እና መተንተን አለበት፡፡

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ረ ሥር የተገለጸው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስፔክተሩ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን የሚፈልጉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በኢንስፔክሽኑ ላይ የተገኙ አካላት ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ ይችላል፡፡

2/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በሚገኙበት ቦታ ላይ መገኘት ሳያስፈልግ የሚደረግ ልኬታዊ ኢንስፔክሽን የሚከተሉት ጉዳዮችን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡-

ሀ) ኢንስፔክተሩ በዚህ መመሪያ በእዝል 1 ላይ የተደነገጉ የፐርልስ ምጣኔዎች ማወቅ፣

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 በንኡስ-አንቀጽ 1 እስከ 7 የተደነገጉ የመረጃ ምንጮችን ማሟላት፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ 2 ለ ላይ የተገኙ የመረጃ ምንጮችን ከተቀመጠው ስታንደርድ ጋር በማነጻጸር መተንተን እና የውሳኔ ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

መ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ሐ የሚሰጠው የውሳኔ ሀሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 መሠረት ከተቀመጠው የቅጣት ደረጃ ጋር በማነጻጸር ይቀጣል ፣

f) The inspector shall inspect the saving and credit cooperatives by examining and analyzing the sources of information in article 15 sub articles 1 up to 7 of this directive;

g) Subject to the provisions of sub-article 1 (f) of this article, the Inspector may, in the event of any further clarification, request the relevant parties and those present at the inspection to provide clarification;

2/ Off-Site inspection of saving and credit cooperatives should be based on the following factors:

a) Maintain and understand the specific criteria set out in annex 1 of this directive, which are favored by our country's saving and credit cooperatives;

b) Comply with the sources provided for in article 16, Sub-article 1 to 7 of this directive;

c) Analyze the sources of information obtained in sub-article 2(b) of this article and make recommendations;

d) Without prejudice this article sub-article 2(c), the recommendation regarding a penalty shall be taken by comparing the problems and gaps identified in accordance with article 22 of this directive with the established standard.

የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Archive
Cooperative Agency

## ክፍል አምስት

## ስለ ቅጣት አወሳሰን እና ስለሚሰጥ ግብረ መልስ

### 17. የቅጣት ደረጃዎች

1/ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት በልኬታዊ ኢንስፔክሽን ኢንስፔክት የተደረገ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ተደርገው የተለዩ ክፍተቶች የሚያስከትሉት ጉዳት መሰረት በማድረግ ከባድ፣ መካከለኛ እና ቀላል የቅጣት ደረጃዎች ተብሎ ይቀጣል፡፡

2/ በኢንስፔክተሩ የሚሰጠው ግብረ መልስ የቅጣት ደረጃውን እና የቅጣት አይነቱን በግልጽ ማስቀመጥ አለበት፡፡

3/ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር የኅብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቅጣት ለሚመለከተው የመንግስት ፋይናንስ መስሪያ ቤት ገቢ የሚደረግ ይሆናል፡፡

4/ ከተመረጡት 10 የፐርልስ ስታንደርድ ምጣኔዎች ተመዝኖ አብላጫው አፈፃፀሙ ከባድ ቅጣት ደረጃ ላይ ከወደቀ ከባድ ቅጣት ይቀጣል፣

5/ ከተመረጡት 10 የፐርልስ ስታንደርድ ምጣኔዎች ተመዝኖ አብላጫው አፈፃፀሙ መካከለኛ ቅጣት ደረጃ ላይ ከወደቀ መካከለኛ ቅጣት ይቀጣል፣

6/ ከተመረጡት 10 የፐርልስ ስታንደርድ ምጣኔዎች ተመዝኖ አብላጫው አፈፃፀሙ ቀላል ቅጣት ላይ ከወደቀ ቀላል ቅጣት ይቀጣል፣

## PART FIVE

## ABOUT PENALTY AND FEEDBACKS

### 17. Penalty Classification

1/ Saving and credit cooperative societies shall be inspected prudentially, and depending on the gaps and risks identified, penalties shall be classified as 'grave,' 'medium' and 'simple'

2/ The feedback shall be given to prudentialy inspected saving and credit cooperatives and shall include clear type and class of the penalty as applicable.

3/ If the performance of the majority of the 10 selected PEARLS standard ratio falls in the grave category, a severe measure shall be imposed.

4/ If the performance of the majority of the 10 selected PEARLS standard ratio falls in the moderate level, a moderate penalty shall be imposed.

5/ If the performance of the majority of the 10 selected PEARLS standard ratio falls in the simple category, simple measures shall be imposed.

6/ If the steps referred to in sub-articles 3 to 5 of this article get equal points, or lay in different penalty classes, the type of penalty to be imposed shall be determined by the inspector.



Archive
Cooperative

7/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 ፣5 ፣6 የተጠቀሱት የቅጣት ደረጃዎች እኩል ነጥብ ያገኙ ከሆነ ወይም አፈጻጸሙ በተለያየ የቅጣት ደረጃ ላይ ከወደቀ የሚወሰደው የቅጣት ደረጃ በኢንስፔክተሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

18. <u>በፐርልስ ምጣኔ ልኬት መሰረት ስለሚወሰድ ቅጣት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 መሰረት የሚያስከትለው ቅጣት ዓይነት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ ከባድ ቅጣት የተወሰደበት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለአንድ ጊዜ ብቻ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) የሚቀጣ ሆኖ የታዩበትን ክፍተቶች 3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በማስተካከል አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ አለበት፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰውን ቅጣት ተግባራዊ ማድረግ የማይችል የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር 3 ወሩ እንዳለቀ በ 1ወር ጊዜ ውስጥ ከሥራ እንቅስቃሴው ይታገዳል፤ በተጨማሪ በአንድ ወር ጊዜ ተሰጥቶት ማስተካከል ካልቻለ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡

3/ መካከለኛ ቅጣት የተወሰነበት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለአንድ ጊዜ ብር 2,000 (ሁለት ሺ ብር) የሚቀጣ ሆኖ የታዩበትን ክፍተቶች 3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በማስተካከል አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሰውን ቅጣት ተግባራዊ ማድረግ የማይችል የገንዘብ ቁጠባና

7/ If the steps referred to in sub-articles 4,5,6 of this article get equal points,or lay on different penalty classes ,the type of penalty to be taken shall be determined by the inspector.

18. **<u>Penalties Based on PEARLS Ratio</u>**

The type of penalty to be taken in accordance with article 17 of this directive shall be as follows:-

1/ The saving and credit cooperative societies, which have been severely punished, shall be punished with a fine of Birr 5,000 (five thousand birr) and shall report the deficit within three months to the appropriate authority.

2 / A saving and credit cooperative societies that fails to implement the penalty referred to in sub-article 1 of this article shall be suspended from its activities within 1 month after the expiration of 3 months. In addition, if it is not paid within a month, it will be closed down.

3/ A saving and credit cooperative societies which have been medium punished, shall be fined Birr 2,000 (two thousand Birr) and shall correct the deficit within three months and report the progress to the appropriate authority.

4 / A saving and credit cooperative societies that



Cooperative Agency
Archive

ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር 3 ወሩ እንዳለቀ በተጨማሪ በ2 ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክል የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ሆኖ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሊያስተካከል ካልቻለ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚቀጣ ይሆናል፣

5/ ቀላል ቅጣት የተወሰደበት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የታዩበትን ክፍተቶች 3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በማስተካከል ሪፖርት እንዲያደርግ ይደረጋል፣ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ በቅደም ተከተል በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1፣2፣ 3 መሠረት የሚቀጣ ይሆናል ።

## 19. <u>ሪፖርት አለመላክ ስለሚያስከትለው ቅጣት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለልኬታዊ ኢንስፔክሽን የሚያስፈልገውን ሪፖርት በተጠቀሰው ጊዜ ካላቀረበ በኢንስፔክተሩ የሚከተሉትን ቅጣቶች ይቀጣል።

1/ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ካልላከ 1000 ብር ቅጣት እና የመጀመሪያ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የተቀጣ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር የኅብረት ስራ ማህበር ከተቀጣበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀን ውስጥ ሪፖርቱን ካላቀረበ ለሁለተኛ ጊዜ 2000 ብር ቅጣት እና የመጨረሻ ማስጠንቀቅያ ይሰጠዋል።

fails to implement the penalty based on sub-article 3 of this article shall be given a final warning within 2 months after the end of the month.

5/ A saving and credit cooperative societies, which have been given a simple penalty, will be required to report the shortcomings within three months. If it fails to make amends within the allotted time, action shall be taken in accordance with sub-articles 1, 2, 3 of this article respectively.

## 19. <u>Penalty for non-submission of a report</u>

Subject to article 7, sub-article 4 of this directive, if the saving and credit cooperative society does not submit the required report for the prudential inspection within the specified time;

1/ If not submitting the report within the specified time, an initial written warning shall be issued with a fine of Birr 1000 (one thousand Birr) for the first time.

2/Based on this article sub article 1 penailized saving and credit cooperative failing to submit the report from penailized day up to thirty consecutive days , a second time, shall pay fee Birr 2,000 (two thousand Birr) and be given a final warning



Cooperative Agency

| | |
|---|---|
| 3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኀብረት ስራ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ወይም የተወከለ ሰራተኛ በኅብረት ስራ ማህበሩ የሰው ሀብት ልማት መመሪያ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡ | 3/ Without prejudice of this article, sub article 1and 2 disciplinary penalty shall apply to the cooperative society manager or to a representative employee in accordance with cooperative Human Resource Development Directive. |
| 4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ካላቀረበ ለአንድ ወር ከሥራው ይታገዳል፡፡ | 4/ Failure to comply in accordance with sub-article 2 of this article; it shall be suspended for one month. |
| 5/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ እግዱ እንዲነሳለት እግዱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ አስተካክሎ አግባብ ላለው ባለስልጣን ካላቀረበ ህጋዊ ሰውነቱን ያጣል፡፡ | 5/ Without prejudice to this article sub article 4 saving and credit cooperative shall lose its legal identity if it does not submit a suspension leave application to the appropriate authority within fifteen consecutive days from the date of suspension. |
| **20. <u>በኢንስፔክሽን ሥራ ላይ እንዲገኙ የሚፈለጉ አካላትን አለማቅረብ ስለሚያስከተለው ቅጣት</u>** | **20. <u>Penalty for the failure to ensure the attendance of nominated persons during an inspection</u>** |
| በዚህ መመሪያ አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 1(ሐ) በቦታ ላይ በሚደረገው የልኬታዊ ኢንስፔክሽን ሥራ ላይ እንዲገኙ የሚፈለጉ አካላትን በተባለው መሠረት ማቅረብ የማይችል የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉትን የቅጣት አይነቶችን ይቀጣል፡- | A saving and credit cooperative society that is unable to provide the required persons to participate in the on-site prudential inspection in accordance with Article 16, Sub-Article 1 (c) of this directive shall be penalized, and the penalty type is as follow :- |
| 1/ በመጀመሪያ 500 (አምስት መቶ ብር) ተቀጥቶ የሚፈለጉ ሰዎችን በቀጣይ ሰባት ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ | 1/ For the first time a 500 (five huondred Birr) fine will be imposed along with an instraction to present the required persons within the next seven days. |

2/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የኀብረት ስራ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ወይም ተወካይ ቅጥር ሰራተኛ በኀብረት ስራ ማህበሩ የሰው ሀብት ልማት መመሪያ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አቀጽ 1 መሰረት በሰባት ቀን ውስጥ ካላቀረበ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ከሥራው ይታገዳል ፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አቀጽ 3 መሰረት እግዱ ከታገደበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ እግዱ እንዲነሳለት የተባለውን አሟልቶ ካልቀረበ ህጋዊ ሰውነቱን ያጣል፡፡

21. <u>በልኬታዊ እና በኢልኬታዊ ኢንስፔክሽን መመሪያ መሰረት ስለሚደረግ ኢንስፔክሽን</u>

1/ በልኬታዊ አሰራር ኢንስፔክት የሚደረጉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በኢ-ልኬታዊ አሰራር ጭምር ኢንስፔክት ተደርገው ክፍተቶች ከታዩበት በኢልኬታዊ ኢንስፔክሽን መመሪያ ላይ በተቀመጡ የቅጣት አይነቶች መሠረት የሚቀጣ የሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በተመሳሳይ ጊዜ በልኬታዊ እና ኢ-ልኬታዊ የኢንስፔክሽን አሰራር ተመዝኖ የተለያየ የቅጣት ዓይነት እንደሚወሰድ ካመላከተ በኢንስፔክተሩ የሚወስነው የቅጣት ዓይነት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

2/ Without prejudice of this article, sub article 1 disciplinary measures shall be taken on the cooperative manager or representative employee in accordance with the Cooperative Human Resource Development Directive.

3/Based on this article sub-article 1 the cooperative failing to bring the responsible person shall be suspended.

4/ Based on this article sub-article 3 the saving and credit cooperative that does not submit a suspetion leave application with in fifteen consecutive days from the day the suspension was initiated, shall lose its legal personality.

**21. <u>Inspection done based on Prudential and non Prudential directive</u>**

1/Prudentially inspected saving and credit cooperatives shall have other failings after being inspected non prudentially, shall be penalized based on non prudential inspection directives

2/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this article, if a saving and credit cooperative inspection which involves prudential and non-prudential inspection methods and concludes that a different penalty should apply, the penalty thus determined by the inspector shall prevail applied .



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Cooperative Agency

22. **<u>በልኬታዊ የኢንስፔክሽን አሰራር ኢንስፔክት የተደረጉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ የታዩ ክፍተቶች በኢንስፔክተሩ የሚወሰደው ቅጣት ደረጃ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡-</u>**

| ኮድ | ቀመር | ግብ | የቅጣት ደረጃ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከባድ | መካከኛ | ቀላል |
| P1 | ለማይመለስ ብድር መጠባበቂያ አቅርቦት ሲካፈል የመመለሻ ግዜው 12 ወራት ያለፈው እና ገና ያልተሰረዙ ብድሮች | 100% | <70% | 70-79.99% | 80-95% |
| P6 | የንብረቶች ዋጋ ሲካፈል አጠቃላይ የአባል ዕጣ ድርሻ እና ተቀማጭ ገንዘብ | >110% | <100% | 100-104.99% | 105-108% |
| E1 | የተጣራ ብድሮች ሲካፈል ለጠቅላላ ሃብቶች | ከ70-80% | <5% &>85% | 50-59.99% | 60-65% |
| E2 | ጥሬ ገንዘብ ሲካፈል ጠቅላላ ሃብቶች | ከ10-20% | <5 >30% | 5-7%& 25 - 30% | 7.1-9.99% &< 20.1-24.99% |
| E5 | ቁጠባዎች እና ተቀማጭ ገንዘብ ሲካፈል ጠቅላላ ሃብቶች | ከ70-80% | <50% | 50-59.990% | 60-65% |
| E8 | ተቋማዊ ካፒታል ሲካፈል ጠቅላላ ሃብቶች | ≥ 10% | <4% | 4-6.99% | 7-9% |
| A1 | ጠቅላላ ያልተመለሰ ብድር ሲካፈል የመመለሻ ግዜው የደረሰ ብድር መጠን | ≤ 5% | >7% | 6-7% | 4-5.99% |
| R9 | የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲካፈል ጠቅላላ አማካይ ሃብቶች | ≤ 5% | >7% | 6-7% | 5.1-5.99% |
| L1 | ጠቅላላ ጥሬ ገንዘብ ሃብቶች ( ገቢ የሚያስገኙ እና ገቢ የማያስገኙ ሃብቶች ድምር) ሲቀነስ የአጭር ጊዜ ግዴታዎች ሲካፈል ጠቅላላ ዕጣ እና ቁጠባ | ቢያንስ 15% | < 5% | 5-10% | 10.1-14.99% |
| S10 | የአባላት ዕድገት | >12% | < 5% | 5-7.99% | 8-10% |

22. **<u>The weaknesses in the saving and credit cooperatives shall be inspected by the prudential inspection system,and where they fall below the nominated standards and fail to amend the problem/s a penalty shall be levied by the inspector on the following basis;</u>**

| Code | Formula | Goal | Level of penalty to be taken | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | Grave | medium | simple |
| P1 | Allowance for Loan Losses / Delinquency >12 months | 100% | <70% | 70-79.99% | 80-95% |
| P6 | Solvency (Net Value of Assets/Total Shares and Deposits) | >110% | <100 % | 100-104.99% | 105-108% |
| E1 | Net Loans/Total Assets | 70-80% | <50% & >85% | 50-59.99% | 60-65% |
| E2 | Liquid Investments/Total Assets | 10-20% | <5 >30% | 5-7%& 25 - 30% | 7.1-9.99% &< 20.1-24.99% |
| E5 | Saving Deposits/Total Assets | ከ70-80% | <50% | 50-59.990% | 60-65% |
| E8 | Institutional Capital/Total Assets | ≥ 10% | <4% | 4-6.99% | 7-9% |
| A1 | Total Loan Delinquency/Gross Loan Portfolio | ≤ 5% | >7% | 6-7% | 4-5.99% |
| R9 | Total Administrative Expenses/Avg.Total Assets | ≤ 5% | >7% | 6-7% | 5.1-5.99% |
| L1 | Liquid investments [Short Term Investments] + Liquid Assets ( - ) Short Term Payables / Saving Deposits | Min.15 % | < 5% | 5-10% | 10.1-14.99% |
| S10 | Growth in Membership | >12% | < 5% | 5-7.99% | 8-10% |



የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
Cooperative Agency

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**23. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛዉም ሰው ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

**24. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች**

ይህንን መመሪያ የሚጻረር እና የሚቃረን መመሪያ፣ ልማዳዊ አሰራር እና በመተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ ውስጥ የተቀመጠ አንቀጽ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፣

**25. ስለመመሪያው መሻሻል**

ይህ መመሪያ እንዳስፈላጊነቱ በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ሊሻሻል ይችላል።

**26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን 4/1/2014 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፣

አዲስ አበባ መስከረም 4 ቀን 2014 ዓ.ም

ኡስማን ሱሩር ሲራጅ
የፌዴራል ኅብረት ስራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**23. Obligation to cooperate,**

Everyone has a duty to cooperate in enforcing this directive.

**24. Inapplicable laws**

Any directive or customary practice, provision of by-laws and internal rule of cooperatives that is inconsistent with this Directive shall not be applicable.

**25. Amendment of the directive**

This directive shall be amended by the Federal Cooperative Agency as needed.

**26. Effective date**

This directive shall be effective beginning from 14/9/ 2021 G.C.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of September 2021**

Usman Surur Siraj
The Director General of Federal Cooperative Agency

## እዝል፡-1. በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራዊ የሚደረጉ የ"መውጥምክእ" ልኬታዊ የቁጥጥር ምጣኔዎች

| ተቁ | የመለኪያው ዓይነት | የመለኪያው መለያ /ኮድ | ቀመር | ግብ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ጥበቃ ማድረግ( ሃብት ወይም ንብረት) | መ1. | ለማይመለስ ብድር መጠባበቂያ አቅርቦት **ሲካፈል** የመመለሻ ጊዜው 12 ወራት ያለፈው እና ገና አልተሰረዙ ብድሮች | 100 % |
| | | መ6 | የንብረቶች ዋጋ **ሲካፈል** አጠቃላይ የአባል ዕጣ ድርሻ እና ተቀማጭ ገንዘብ | >110 |
| 2. | ውጤታማ የፋይናንስ አወቃቀር | ው1 | የተጣራ ብድሮች **ሲካፈል** ለጠቅላላ ሃብቶች | 70-80% |
| | | ው2. | ጥሬ ገንዘብ **ሲካፈል** ጠቅላላ ሃብቶችት | ከ10-20% |
| | | ው5. | ቁጠባዎች እና ተቀማጭ ገንዘብ **ሲካፈል** ጠቅላላ ሃብቶች | 70-80% |
| | | ው8 | ተቋማዊ ካፒታል **ሲካፈል** ጠቅላላ ሃብቶች | ≥10 % |
| 3. | የሃብት (የንብረት ) ጥራት | ጥ1. | ጠቅላላ ያልተመለሰ ብድር **ሲካፈል** የመመለሻ ግዜው የደረሰ ብድር መጠን | ≤ 5% |
| 4. | የገቢና ወጪ ምጣኔ | ም9. | የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች **ሲካፈል** ጠቅላላ አማካይ ሃብቶች | ≤ 5% |
| 5. | የመክፈል አቅም | ክ1. | ጠቅላላ ጥሬ ገንዘብ ሃብቶች ( ገቢ የሚያስገኙ እና ገቢ የማያስገኙ ሃብቶች ድምር) ሲቀነስ የአጭር ጊዜ ግዴታዎች **ሲካፈል** ጠቅላላ ዕጣ እና ቁጠባ | ≥ 15% |
| 6. | የእድገት ምልክት | እ10. | የአባላት ዕድገት | > 12% |

## Annex-1- Pearls applied by saving and Credit Cooperative society of prudential regulation control rates

| no. | the type of measurement | code | formula | goal |
|---|---|---|---|---|
| 1 | protection | P1. | allowance for loan losses / delinquency >12 months | 100% |
| | | P6. | solvency (net value of assets/total shares and deposits) | >110 |
| 2 | effective financial structure | E1 | net loans/total assets | 70-80% |
| | | E2 | liquid investments/total assets | 10-20% |
| | | E5 | saving deposits/total assets | 70-80% |
| | | E8 | institutional capital/total assets | ≥10% |
| 3 | asset quality | A1. | total loan delinquency/gross loan portfolio | ≤5% |
| 4 | rates of return and costs | R9. | total administrative expenses/avg.total assets | ≤5% |
| 5 | liquidity | L1. | liquid investments [short term investments] + liquid assets ( - ) short term payables / saving deposits | ≥ 15% |
| 6 | sign of growth | S10. | growth in membership | > 12% |



Cooperative Agency

**እዝል፡- 2. የሃብትና ዕዳ መግለጫ፤**

| **ሀብትና ዕዳ መግለጫ** | |
|---|---|
| **ሃብት በብር** | |
| በእጅ የሚገኝ ገንዘብ/ጥሬ ገንዘብ በእጅ/ | |
| በባንክ የሚገኝ ገንዘብ | |
| ለአባላት የተሰጠ ብድር | |
| *ለማይመለስ ብድር መካ* | |
| *የተቀነሰ ገንዘብ* | |
| ኢንቨስትመንት (የዓመቱ ብቻ) | |
| ኢንቨስትመንት (ከአንድ ዓመት በላይ) | |
| ቋሚ ሃብት | |
| *የተቀናሽ የእርጅና ተቀናሽ* | |
| **አጠቃላይ ሃብት** | |
| **ዕዳ በብር** | |
| መደበኛ የአባላት ቁጠባ | |
| እጣ | |
| የፍላጎት ቁጠባ | |
| የባንክ ብድር | |
| ሌሎች ብድር | |
| የሚከፈሉ ወጭዎች | |
| **አጠቃላይ ወጭ** | |
| **ካፒታል በብር** | |
| የመጠባበቅያ ፈንድ | |
| ለአባላት ከሚከፋፈለው | |
| ትርፍ የቀረ ገንዘብ | |
| የዓመቱ ትርፍ/ኪሳራ | |
| የማህበራዊ አገልግሎት ፈንድ | |
| የአባላት ዕጣ | |
| **አጠቃላይ ካፒታል** | |
| **አጠቃላይ ዕዳ እና ካፒታል** | |

**Annex-2- Balance Sheet**

| **Balance Sheet** | |
|---|---|
| **Assets** | |
| **Birr** | |
| Cash On Hand | |
| Cash At Bank | |
| Loans To Members | |
| *Less Loan Loss Reserve* | |
| Investments (Under One Year) | |
| Investments (Over One Year) | |
| Fixed Assets | |
| *Less Accumulated Depreciation* | |
| **Total Assets** | |
| **Liabilities** | |
| **Birr** | |
| Compulsory Saving | |
| Withdrawable shares | |
| Voluntary Saving | |
| Bank Borrowings | |
| Other Borrowings | |
| Accrued Expenses | |
| **Total Liabilities** | |
| **Capital** | |
| **Birr** | |
| Reserve Fund | |
| Retained Earnings | |
| Current Year's Surplus/(Deficit) | |
| Social Fund | |
| Member's Shares | |
| **Total Capital** | |
| **Total Liabilities And Capital** | |

# የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ ለማስቀመጥ
# የተዘጋጀ መስፍርት

መስከረም 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዝገብ ቤት
Archive
Cooperative Agency

1. የስታንደርዱ መነሻዎች
   - የሚያከናውነት አንኳር ተግባር ዓይነት፣
   - የሚያከናውኑት ተግባር በአባላት ተጠቃሚነት እና በአገር ዕድገት ላይ የሚኖረው አስተዋጽዖ፣
   - በዜጎች ተጠቃሚነት ላይ የሚኖረው አስተዋጽዖ፣

2. ለመስፈርቱ የተቀመጡ ከፍተኛ መመዘኛ ቁጥሮች መነሻ
   - የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ አገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃ ቋት (Data base) በ2012 ዓ.ም ያስጠናው የጥናት ውጤት፣
   - በየክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ እስከ 2012 ዓ.ም የተጠናቀሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃዎች፣
   - በተለያዩ ወቅቶች ከኅብረት ሥራ ማህበራት የተገኙ ተጨባጭ መረጃዎች፣

3. አከባቢን መሠረት አድርገው በገጠር የተደራጁ ገንዘብ ቁጠበና ብድር መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የደረጃ መለያ መስፈርት

| ተ.ቁ | መመዘኛ መስፈርቶች | መለኪያ | ከፍተኛው መጠን | ክብደት በመቶኛ | ያገኘው ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአባላት ብዛት፣ | ቁጥር | 1000 | 20 | | |
| 2 | የተሰበሰበ የቁጠባ መጠን፣ | በሚሊ. ብር | 10 | 20 | | |
| 3 | ያፈሩት ካፒታል መጠን፣ | በሚሊ. ብር | 3 | 15 | | |
| 4 | የተሰጠ የብድር መጠን | በመቶኛ | 70 | 20 | | |
| 5 | ብድር ያገኙ አባላት ብዘት፣ | በመቶኛ | 10 | 10 | | |
| 6 | የብድር አመላለስ | በመቶኛ | 98 | 5 | | |
| 7 | የተቀጠሩ ሰራተኞች ብዛት፣ | ቁጥር | | 10 | | |
| 7.1 | ቋሚ | ቁጥር | 7 | 6 | | |
| 7.2 | ጊዜያዊ | ቁጥር | 60 | 4 | | |
| | ድምር | | | 100 | | |

4. አከባቢን መሠረት አድርገው በከተማ የተደራጁ ገንዘብ ቁጠበና ብድር መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የደረጃ መለያ መስፈርት

| ተ.ቁ | መመዘኛ መስፈርቶች | መለኪያ | ከፍተኛው መጠን | ክብደት በመቶኛ | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአባላት ብዛት፣ | ቁጥር | 1,000 | 20 | |
| 2 | የተሰበሰበ የቁጠባ መጠን፣ | በሚሊ. ብር | 20 | 20 | |
| 3 | ያፈሩት ካፒታል መጠን፣ | በሚሊየን ብር | 3 | 15 | |
| 4 | የተሰጠ የብድር መጠን | በመቶኛ | 70 | 20 | |
| 5 | ብድር ያገኙ አባላት ብዘት፣ | በመቶኛ | 10 | 10 | |
| 6 | የብድር አመላለስ | በመቶኛ | 98 | 5 | |
| 7 | የተቀጠሩ ሰራተኞች ብዛት፣ | ቁጥር | | 10 | |
| 7.1 | ቋሚ | ቁጥር | 7 | 6 | |
| 6.2 | ጊዜያዊ | ቁጥር | 60 | 4 | |
| | ድምር | | | 100 | |

የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዝገብ ቤት
Archive
Cooperative Agency

## 5. ተቋሚን መሠረት አድርገው የተደራጁ ገንዘብ ቁጠበና ብድር መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የደረጃ መለያ መስፈርት

| ተ.ቁ | መመዘኛ መስፈርቶች | መለኪያ | ከፍተኛው መጠን | ክብደት በመቶኛ | ያገኘው ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአባላት ብዛት፣ | በመቶኛ | 90 | 20 | | |
| 2 | የተሰበሰበ የቁጠባ መጠን፣ | በሚሊየን ብር | 50 | 20 | | |
| 3 | ያፈሩት ካፒታል መጠን፣ | በሚሊየን ብር | 20 | 15 | | |
| 4 | የተሰጠ የብድር መጠን | በመቶኛ | 70 | 20 | | |
| 5 | ብድር ያገኙ አባላት ብዘት፣ | በመቶኛ | 10 | 10 | | |
| 6 | የብድር አመላለስ | በመቶኛ | 98 | 5 | | |
| 7 | የተቀጠሩ ሰራተኞች ብዛት፣ | ቁጥር | | 10 | | |
| 7.1 | ቋሚ | ቁጥር | 7 | 6 | | |
| 7.2 | ጊዜያዊ | ቁጥር | 60 | 4 | | |
| | ድምር | | | 100 | | |

## 6. የገንዘብ ቁጠበና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን የደረጃ መለያ መስፈርት

| ተ.ቁ | መመዘኛ መስፈርቶች | መለኪያ | ከፍተኛ መጠን | ክብደት በመቶኛ | ያገኘው ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአባላት ብዛት | በመቶኛ | 95 | 10 | | |
| 2 | የተሰበሰበ የቁጠባ መጠን፣ | በሚሊየን ብር | 30 | 20 | | |
| 3 | የካፒታል መጠን፣ | በሚሊየን ብር | 30 | 15 | | |
| 4 | የተሰጠ የብድር መጠን | በመቶኛ | 70 | 25 | | |
| 5 | የተቀጠሩ ቋሚ ሰራተኞች ብዛት፣ | ቁጥር | 15 | 10 | | |
| 6 | የብድር አመላለስ | በመቶኛ | 98 | 10 | | |
| 7 | የፋይናንስ አገልግሎት ማስፋፋት | በዓይነት | 5 | 10 | | |
| | ድምር | | | 100 | | |

## 7. ቀመር

ከተቀመጠው ከፍተኛ መጠን በታች አፈጻጸም ያላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤት ከዚህ በታች በተቀመጠው ቀመር መሠረት የሚሰላ ይሆናል፣

**የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያገኘው ውጤት = ያለው አፈጻጸም መጠን Xለመለኪያው የተሰጠው ክብደት**
**ለተቀመጠው ከፍተኛ መጠን**

## 8. ደረጃዎች

- አጠቃላይ ያገኙት ነጥብ፦
  - ከ 80 % እና ከዚያ በላይ ከሆነ ‹‹ሀ›› ወይም አንደኛ ደረጃ ይሆናል፣
  - ከ55---79.99 ከመቶ በላይ ከሆነ ‹‹ለ›› ወይም ሁለተኛ ደረጃ ይሆናል፣
  - ከ 25---54.99 ከመቶ በላይ ከሆነ ‹‹ሐ›› ወይም ሦስተኛ ደረጃ ይሆናል፣
  - ከ25 ከመቶ ነጥብ በታች የሚያገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲፈርሱ ወይም እንዲወሃዱ ይደረጋል፣

በልኬታዊ አሰራር ኢንስፔክት የሚደረጉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ ‹‹ ሀ›› ላይ የሚገኙ ይሆናሉ። እንደአስፈላጊነቱ ወደ ሌሎችም ደረጃዎች በቀጣይ እያቀድን የምንሰራ ይሆናል

የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
መዝገብ ቤት
Archive
Cooperative Agency